# እንዳትሰለች ከቻልክ መልክህን ቀይር

መከሊት እና ጓደኞቹ ከአራዳው ሰፈር

እሁድ ከሰአት በኋላ ነበር የአዲስ አበባ ሞቃታማ አየርን ለመቀየር ወደጎጃም መንገድ ከጓደኞቼ ጋር በህብረት ወጣ ያልነው። አቀበቱን እንደተያያዝን እና አራዳው ጊዮርጊስ ጋር እንደደረስን አንድ ታክሲ እንደልማዱ ሳይታሰብ ከፊታችን ድቅን አለ። እንደተለምዶ የያዝኩት አዲሱ ጠባዬ በየታክሲው መስታዎት ኋላ የሚጻፉትን ፅሁፎች ማንበብ ነው። ይህኛው ጸሁፍ እኔንም ጓደኞዬንም አይናችን ነው ወይስ የጥቅስ ስህተት ነው እየተባባልን ለመቅረብ ስንል አንድ ቦታ ላይ ለትንሽ አደጋ ተጋልጠንም ነበር።
ፅሁፉ " እንዳትሰለች ከቻልክ መልክህን ቀይር...መቀየሪያም አለን" ይላል። አንዲት አነስተኛ ሌላ ፅሁፍ ደሞ ከስሩ ተፅፋለች። ይህንኑ ለማወቅ አንድ ቦታ ላይ ተሳፋሪ ለማውረድ ሲቆም ጓደኞዬ ሮጥ ብሎ አነበበው። እሱም እየሳቀ ወደመኪናው ተመለሰ። ምነው አሳቀህ ምን ይላል ስለው አግራሞትን ተላብሶ ለሪፖርተር ጋዜጣ ነው የሚለው አለኝ። አዎ በትንሿ ታክሲው ላይ የተፃፈችው ፅሁፍ ለሪፖርተር ጋዜጣ ይላል። መልእክቱ ሙሉ ለሙሉ ሲነበብ " እንዳትሰለች ከቻልክ መልክህን ቀይር መቀየሪያም አለን...ለሪፖርተር ጋዜጣ" ይላል። ስልክም አድራሻም የለውም ስነስርአቱ የሚከናወነው እዛው በታክሲ ውስጥ ይመስላል።

ይህ ጋዜጣ ላለፉት በርካታ ወራቶች ቅጥ የለሽ፤ መሰረተ ቢስ እንዲሁም ለምን ቀረብኝ በሚል አንባገነንነት ሊያፈርሰው የማይችለውን ግንብ ደብድቦ ደብድቦ አልቻል ሲለው የታክሲውን አድራሻ ጠይቆ መልኩን ሙሉ በሙሉ ባይቀይርም አሁን ደሞ ባለቤትነቱ የህዝብ በሆነው ባንጋፋው ቅዱስ ጊዮርጊስ ክለብ ላይ አሮጌ ኤሊኮፍተሩን እያዣንበበ ነው። መሬትም በኤሊኮፍተሩ ተማራ አላሳርፍህም ስላለችው ሜዳየለሽ መንደሮችን እየረበሸ ነው። የቀድሞ ፌዴሬሽን አመራር እግር ኳሱን እጉድጓድ ውስጥ ከተው የነበሩት፣ ጊዮርጊስንም አጥፍተው ለመጥፋት አቅደው ከነበሩት አሁንም ከአጥሩ ውጪ ሆነው አዋራ የሚጭሩት፣ ከዚህ ጋዜጣ ጋር ሴራ እየጠነሰሱ እንደሆነ በግልፅ የሚታይ ጉዳይ ነው። በዚህን ሰአት እነዚህ አካሎች አንዱን ደጋፊን በሌላው ላይ እንዲነሳ፤ ሁካታው እንዲያይል፣ አንዱ ደጋፊ ያላለውን አለ እያሉ ተመሳሳይ አሳዛኝ ስራቸውን በስፖርቱ ሜዳ ላይ የራሳቸውን ኳስ እየተጫወቱ ሰላም የሰፈነበትን ቦታ ሰላም በሌለው እጣናቸው ሊያጥኑት እየሞከሩ ነው።

ለመሆኑ እውነት ይህን አንጋፋ የኢትዮጵያ ቅርስ የሆነውን ቅዱስ ጊዮርጊስ በደንቡ ያውቁታል? አይደለም አንዲት ትንሽዬ ጋዜጣ እና አቶ ምነው ስልጣን ቀረብኝ የሚባሉት ይቅርና ፋሽስት ጣልያን ሊያፈርሰው ያልቻለው፤ የደርግ ጉልበት እና ጥላቻ ያላጠፋው፣ የፈረሰኞቹ ደም ከዘር ወደዘር ከትውልድ ወደትውልድ የተተላለፈ ውስጡ በፍቅርና በአንድነት በወፍራም ሰንሰለት የተያያዘ መሆኑን ተረድተውት ይሆን? ከዚህ ቤት የወጡት ታሪካቸው ታላቅ ስራቸው ግዙፍ ለኢትዮጵያ ብቻ ሳይሆን ለአለማችን የተረፉ መሆናቸውንስ አንብበዋል? ይህንን ክለብ ሊያጠፉ የፈለጉ ሁሉ ጠፍተው ታሪክ ሆነው ቀርተዋል። እነ አቶ ጋዜጣ እና እነ አቶ ስልጣኔ ቀረብኝ ታሪክ ውስጥ ለመግባት የፈለጉ ይመስላሉ? ታሪክ ነገርን አታበላልጥም ከእውነት ግን ታሪክ ለመሆን ይመጥኑ ይሆን?

ምን ያድርጉ የዘመኑ ዩኒፎርምን ምቀኝነትን፣ እኔ ከሞትኩ ሰርዶ አይብቀል ባይነትን፣ አሉባልታን ደራርበው ለብሰውታልና የሚሰማቸው እና የሚገባቸው አይመስልም። ጆሮአቸው ተደፍኖአል አይናቸውም ተከድኖአል። ወደትክክለኛው አስተሳሰብ ለመቀየር ቢፈልጉ እንኳን መልካቸው በታክሲው አማካኝነት ይቀየር ይሆናል እንጂ ውስጣቸውን ለመቀየር የሚያስፈልገው መድሃኒት በዚህ አገር እንደማይገኝ ነው የሚወራው። ውጪ መርፌውን ተወግተውት ቢመጡ እንኳን እዚህ ሲደርሱ እንደውሃ መድሃኒቱ ስለሚተን ሁሉም እነሱን ለማዳን አለሁ ያለው በዚህን ሰአት ተስፋ ቆርጦአል። አይደለም ቅዱስ ጊዮርጊስን ሁለት ሰዎችን መለያየት እማይችሉ የዘመኑ ትንሾች ናቸው። ጋዜጠኝነት ምን እንደሆነ ሳይታወቅ ጋዜጠኛ ተኮነ። ኳስ ድቡልቡልነቱ ሳይታወቅ የኳስ መሪ ተኮነ ምን ያድርጉ...አይፈረድባቸውም።
ቅዱስ ጊዮርጊስ ብዙውን ጠላቶቹን ገና ሳያውቃቸው የረገጠ፣ መሰናክሎቹን በየዘመናቱ ያለፈ፣ ነገርን አጥቦ ሳይሆን አስፍቶ የሚያይ፣ ድልን በደስታ ሽንፈትን እጅ ነስቶ የሚቀበል፤ ለኢትዮጵያ ስፖርት ምሰሶ የነበረ አሁንም የሆነ ታሪካዊ ክለብ ነው። ጠላቶቹን ህጋዊ በሆነ መንገድ እስከመጨረሻ ይታገላቸዋል ዝምም ብሎም አያውቅም ወደፊትም አይልም። የጥንት አያቶቻችን የደሙበት የሞቱበት ክለብ ነው። የጋዜጣ እና የቡና ቤት ሴራ አይገታውም አያቆመውም። መሰረቱ የሚያቃጥል አለት ነውና። በስህተት በአለቱ ላይ የማይገባቸው ከቆሙ ይቃጠላሉ። ፈረሰኛው ጊዮርጊስ ምንም አይሆንም እና።
በፈረሱ እንጋልባለን! የፈረሱ ልጓም ለሁሉም ስለማይሆን ፈረሱን ለማታውቁት ተጠንቀቁ
ምንግዜም ጊዮርጊስ
መከሊት እና ጓደኞቹ ከአራዳው ሰፈር